ጥንት፡ጀግኖቻችን፡መንፈስ፡ደንዳና፣
እንዲህ፡ይሉ፡ነበር፡ሀገር፡እንትጠና።
"ሞቸ፡ተነሥቸ፡ልሙት፡እንደ፡ገና፣
አንድ፡ግዜ፡መሞት፡አይበቃንምና"።*፩

# ሰንደቅ፡ዓላማችንን፡

መስከረም፡፲፩፡ቀን፡፳፻፫፡ዓመተ፡ምሕረት።
ገጽ፡፩-፪፤

በኖኅ፡ዘመን፡የጥፋት፡ውኃ፡ማብቂያ፡የተበሠረው፡ቀስተ፡ደመና፡ምልክት፡እንደ፡ነበረ፡ሁልሉ፣ዛሬም፡የዘመነ፡አረመኔው፡ዘረ፡ከሃዲ፡መለስ፡ዚናዊ፡ዐርፎ፡ባሠራው፡ባንዲራ፡ጨርቅ፡ተጠቅልሎ፡በመቀበሩ፡ነባሯ፡ሰንደቅ፡ዓላማችን፡እንደ፡ጥንቱ፡ትመለስ።እናም፣"አረንጓዴ፣ብጫ፣ቀይ፡የኾነው፡የቀስተ፡ደመና፡ምልክት፡በኖኅ፡አማካይነት፡ከእግዚአብሔር፡የተቀበልነው፡የዘለዓለም፡ሰንደቅ፡ዓላማችን፡እንደኾነ፡እንምናለን"።*፪

አረንጓዴ፡ብጫና፡ቀይ፡ሰንደቅ፡ዓላማችን፡የአንድ፡ኢትዮጵያና፡የነፃነት፡ምልክታችን፡ነው።አረንጓዴው፡የአገራችንን፡ልምላሜ፣ብጫው፡ሃይማኖታችንና፡ምግባራችን፣ቀዩ፡ሀገራችን፡ወሰንዋ፡ሳይደፈር፡ነፃነቷ፡ተከብሮ፡እንዲኖር፡ጀግኖች፡ወገኖቻችን፡ለከፈሉት፡መስዋዕትነትን፡የሚገልጽ፡ነው።አረመኔ፡ከሃዲው፡መለስ፡ዚናዊ፡ከከሃዲዎች፡አያቶቹና፡ከከሃዲ፡(ባንዳ)፡አባቱ፡የወረሰውን፡አገር፡አጥፊ፡ተግባሩን፡ሲፈጽም፡ቆይቷል።ታሪኳ፡ተደምስሶ፡ኢትዮጵያን፡ለመበታተን፡በፈጠረው፡የጐሣ፡ፈሊጥ፡(ፖለቲካ)፡ዕቅዱን፡ለመፈጸም፡የሰጣቸው፡የጐሣ፡ባንዲራዎች፡ተጠቅልለው፡ወደ፡ዕቃ፡ቤት፡እንዲገቡ፡ማድረግ፡ነው።መላው፡የኢትዮጵያ፡ተወላጆች፡እንደ፡ጥንቱ፡አንዱ፡ከሌላው፡ሳንለይ፡የሁልላችንም፡የአንድነታችን፡መታዎቂያ፡የሆነው፡አረንጓዴ፣ብጫና፡ቀይ፡ሰንደቅ፡ዓላማችን፡እንደ፡ሆነ፡መርሳት፡የልለብንምና፡ለሀገራችን፡ግርማ፡ሞገሥ፡ሰጪ፡ዓርማ፡እንደ፡ገና፡እንዲውለበለ ብ፡ጫና፡ማድረግ፡ያስፈልገናል።

አዲሱ፡ጠቅላይ፡ምሉክ፡(ሚኒስትር)፡ኃይለማርያም፡ደሳለኝ፡ቃለ፡መሐላ፡በገቡበት፡ወቅት፡የመለስ፡ዚናዊን፡"ራዕይ፡ሳይበረዝ"፡ሥራ፡ላይ፡እንደሚያውሉ፡ተናግረዋል።የርሱን፡አመራር፡ከተከተሉ፡"በእንቅርት፡ላይ፡ጆሮ፡ደግፍ"፡መሆኑ፡ነው።የሀገርን፡ህልውና፡ለማጥፋት፣ኢትዮጵያንና፡ሕዝቧን፡በታማኝነት፡

ጥንት፡ጀግኖቻችን፡መንፈስ፡ደንዳና፣
እንዲህ፡ይሉ፡ነበር፡ሀገር፡እንትጠና።
“ሞቾ፡ተነሥቾ፡ልሙት፡እንደ፡ገና፣
አንድ፡ግዜ፡መሞት፡አይበቃንምና”።*፩

ለማገልገል፡የገቡትን፡መሐላ፡አይርሱ።በመለስ፡ዜናዊ፡ጉደሎ፡አስተሳሰብ፡የተጠነሰሱትን፡ለማቃናት፡መሥዋዕት፡በመሆን፡ፈንታ፤የእርሱን፡ሥራ፡እቀጥላለሁ፡የሚሉ፡ከሆኑ፡በደሉን፡ለመቀጠል፡የተዘጋጁ፡መሆንዎን፡ያስረዳልና፡ከዚህ፡በፊት፡ሥቃይ፡የበዛብን፡እናዝንብዎታለን።በበኩላችን፡የምናሳስብዎ፡ግን፣አይፍሩ።ከሕግ፡ጋራ፡ቆመው፡ወያኔዎችን፡መቋቋምና፡አዘቅት፡ውስጥ፡እስኪ፡ወድቁ፡መሥዋዕት፡መሆን፡ይገባል።ታሪክ፡ሠርቶ፡ማለፍ፡ክብር፡ነው።እነ፡በረከት፡ስምዖን፡መለስ፡ዜናዊ፡በኢትዮጵያ፡ላይ፡የፈጸመውን፡ግፍ፤በዓለም፡አቀፍ፡ደረጃ፡ክብርት፡አና፡ጐሜዝ፡ያጋለጧቸውን፡የመግደል፣የማሠርና፡በእሥር፡ቤት፡የሚፈጸመውን፡ድብደባና፡ሥቃይ፡ለማስተባበል፡ሸሽገው፡ለኢትዮጵያ፡ጥሩ፡ሥራ፡እንደ፡ሠራ፡የሚያናፍሱት፡ወሬ፡ከንቱ፡ውዳሴ፡ነው።እነርሱም፡በቅርቡ፡ጽዋቸውን፡ይቀበላሉ።

በዓለም፡አቀፍ፡ሕግ፡የሀገርና፡ህዝብ፡ሀብት፡የሆነውን፡የአዶላን፡(ሻኪሶ)የወርቅ፡ሀብትና፡ሌላም፡የማዕድንሀብት፡ለሃያ፡አንድ፡ዓመታት፡አላሙዲ፡ወደ፡ውጭ፡አገር፡ሲያግዝ፡ቆይቷል።መቼም፡የከሃዲው፡አረመኔ፡መለስ፡ዜናዊ፡ጥቅም፡ተካፋይ፡“ቀኝ፡ዕጀን፡እንደ፡ተቆረጥኩ፡እቆጥረዋለሁ፡ያለለት፡ቀኝ፡ዕጁ”፡መሆኑ፡ሳይታለም፡የተፈታ፡ነው።አሁን፡መለስ፡ዜናዊ፡የኢትዮጵያ፡አምላክ፡ከከሃዲ፡ጓደኛው፡አባ፡ገብረመድኅን፡ጋራ፡ሆነው፡አልፈዋል።እንግዲህ፣የወርቁና፡የዕብነ፡በረድ፡ሌላም፡የማዕድን፡ሀብት፡አላሙዲ፡ከመበዝበዙ፡አቁሞ፡ለሃያ፡አንድ፡ዓመታት፡የወሰደውም፡እንዲመረመር፡ከማድረግ፡አዲሱ፡አመራር፡ቸል፡እንዳይል፡ኢትዮጵያውያን፡ዜግነት፡ግዴታችን፡ስለ፡ሆነ፡በጥብቅ፡እናሳስባለን።መለስ፡ዜናዊ፣ዓዜብ፡መስፍን፣ስብሐት፡ወልደ፡ሥላሴ፡ነጋ፣በረከት፡ስምዖን፡.......ሌሎች፡ወያኔዎችና፡ተለጣፊዎቻቸውም፡ከኢትዮጵያ፡ሕዝብ፡ዘርፈው፡በልዩ፡ልዩ፡አገር፡ቤተ፡ንዋይዎች፡(ባንኮች)፡ያስቀመጡት፡በሺ፡አእላፍ፡(በቢሊዮን)፡የሚቆጠረው፡ገንዘብ፡ዘረፋን፡የሚቆጣጠረው፡የዓለም፡ሕግ፡ለተጠቃሚው፡የኢትዮጵያ፡ሕዝብ፡እንዲመለስልን፡

ጥንት፡ጀግኖቻችን፡መንፈሰ፡ደንዳና፣
እንዲህ፡ይሉ፡ነበር፡ሀገር፡እንትጠና።
“ሞቾ፡ተነሥቾ፡ልሙት፡እንደ፡ገና፣
አንድ፡ግዜ፡መሞት፡አይበቃንምና”።*፩

የሚያደርግበትን፡ቀን፡ሩቅ፡ላይሆን፡ይችላልና፡የኢትዮጵያ፡ሕዝብ፡ሆይ!፡አይዞን፡እንበ ርታ፡እንላለን።

## ቸሩ፡አምላክ፡ኢትዮጵያንና፡ሕዝቧን፡ይጠብቀን።አሜን።

ከዜናማርቆስ፡መርሐ፣
ሰሜን፡አመሪካ።
እ፡ጦማር፡- E-mail:- zienamarqos14@gmail.com

*፩፡- ክቡር፡ባሕር፡ኃይል፡መኰንን፡አሰፋ፡ሰይፉ፡በጀግኖቻችን፡የተነገረውን፡መቷ፡ምናለሽ፡በኢሳት፡፡
*፪፡- ገጽ፡፩፻፹፱፤ ኢትዮጵያ፡የዓለሙ፡መፋረጃ፡- በንቡረ፡ዕድ፡ኤርምያስ፡ከበደ፡ወልደ፡ኢየሱስ።